# ፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮ የተሳካ የገንዘብ ማሰባሰቢያና የመዝናኛ ዝግጅት አካሄደ!!

የፍኖተ ዴሞክራሲ÷ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ራዲዮ ደጋፊዎች በቶሮንቶ÷ ካናዳ ስኬታማ የሆነ የገንዘብ ማሰባሰቢያና የመዝናኛ ዝግጅት አካሂደዋል። ዝግጅቱ የተካሄደው ማርች 16/2008 ሲሆን ሥነሥርዓቱ ከ2 ፒኤም ጀምሮ እስከ ምሽቱ 10 ሰዓት ድረስ የዘለቀ ነበር። በዚህ የተዋጣለት ዝግጅት ላይ ታዋቂው ገጣሚ አቶ አሊ ሁሴን ተሳታፊ የነበሩ ሲሆን ራዲዮኑን ለመርዳት ለተገኙት በዛ ያሉ ደጋፊዎች አጭር መግለጫና ማበረታቻ ሰጥተዋል።




*አቶ አሊ ሁሴን በእንግዶቹ ጠረጴዛ ዙሪያ ተገኝተው ሃሳቦቻቸውን ሲቀበሉና ሲያወያዩ*

አቶ አሊ ሁሴን ባስተላለፉት አጭር መልእክት÷ ፍኖተ ራዲዮ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ውስጥና በጎረቤት ሀገሮች ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ የሚደመጥ ገልጠው ለሚካሀደው የሰላምና ዴሞክራሲ ትግል ከፍተኛ የዜና ስርጭት አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን አብራርተዋል። ከዚህ

ጋር አያይዘውም፥ የራዲዮኑ አገልግሎት እየጎለበተና ጠቀሜታው እየጎላ በመምጣቱ በአሁኑ ሰዓት ከተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች ሰፊ ድጋፍ እያገኘ መምጣቱን አጽንኦት ሰጥተው አስረድተዋል። ይህም ራዲዮኑን እስካሁን ታግለው ያቆዩትንና ያስቀጠሉትን በእጅጉ ያስደሰተ መሆኑን ጠቁመው፥ በአጠቃላይም ወያኔ የዘጋውን የነጻ ፕሬስ ሚና ከሞላ ጎደል ሸፍኖ በመገኘቱ አገር ወዳድ ዜጋን ሁሉ አስደስቷል ብለዋል።

አቶ አሊ ሁሴን ለተሰብሳቢዎቹና ደጋፊዎቹ ባሳሰቡት ቁምነገር ላይ፥ ፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮን ማስቀጠል የእያንዳንዱ ሀገር ወዳድ ዜጋ ሃላፊነት መሆኑን አመልክተው፥ ሁሉም በያለበት የፍኖቴ ራዲዮ ድጋፍ ኮሚቴ በማቋቋም የተቻለውን ሁሉ ማበርከት ይችላል ብለዋል።

በቶሮንቶ ከተማ ውስጥ በዕለቱ አስገራሚ ዜና ሁኖ የዋለው ጉዳይ፥ በዚሁ እለት በተመሳሳይ ሰዓት ከኢሕአፓ በፈቃዳቸው ጉባኤ ረግጠው የወጡት ወገኖች ክፍል አደናጋሪ የሆነ ስብሰባ ጠርቶ መዋሉ ነው። ይህ ክፍል በእርግጥም ሕዝባዊ ትግሉ እንዳይራመድና ስኬታማ እንዳይሆን ምን ያህል ታጥቆ እንደሚንቀሳቀስ በተግባሩ በማረጋገጡ፥ በአካባቢው በትግል ተሳትፏቸውና በተባባሪነታቸው የሚታወቁ መልካም አሳቢ ወገኖች ሁሉ “ወዮው ጉድ” ብለዋል። ከሁሉም የሚገርመው ደግሞ፥ ከተገኘ መረጃ ማወቅ እንደተቻለው፥ ወደ ራዲዮኑ የድጋፍ ዝግጅት ይመጡ የነበሩ ወገኖችን መንገድ ላይ በመቀበልና አሳሳች የሆነ አድራሻ በመስጠት እንግዶች ወዳላሰቡት ነገር ግን ይኸው ከኢሕአፓ የወጣው ንዑስ ክፍል ወደሚያካሂደው ስብሰባ በመምራት ግራ ሲያጋቡ ውለዋል። በንኡሳኑ ስብሰባ ላይ የተገኙት አብዛኞቹ ይህን በመሳሰለ መንገድና “ኢሕአፓ ነን” በሚል ስም በመጠቀም ያላወቁ ያልጠረጠሩ “የቤት ልጆች” የመጡ ሲሆን፥ በአንጻሩ ደግሞ የኢሕአፓ መዳከም ድል የሚመስላቸው አንድ ሁለት አውቆ አጥፊዎች መገኘታቸውን ማወቅ አልከበደም። በተረፈ ግን ንክኪ በንክኪ እርስ በርሳቸው ተጠራርተው “አይዞን አይዞን” ተባብለው መለያየታቸውን በትዝብት አዳምጠናል።

በበኩላችን፥ ለዴሞክራሲና ለፍትህ ርትእ የሚደረገው ትግል እንዲቀጥልና የአንድነት ሃይሉ እንዲጠናከር፥ ፍኖተ ዴሞራሲ ራዲዮንና መሰል የብዙሃን መገናኛዎችን በቋሚነት ለመደገፍ ቃል እንገባለን። የታጋዩን አንድነት የሚያመነምኑና የሕዝብን ተስፋ የሚያጨልሙ እልኸኞችና 'ከራስ ወዲያ ሰማይ' ባዮች ማንንም ከማይጠቅመው አድራጎታቸው እንዲቆጠቡ በዚህ አጋጣሚ ማስገንዘብ እንወዳለን።

አንድነት ሃይል ነው!
የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል

በቶሮንቶ(ካናዳ) የፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮ ደጋፊዎች